Department of Health

# ስለ ኤፍ ጂ ኤም ተጨማሪ መረጃ

የሴቶች ሀፍረተ ስጋ መግረዝ (ኤፍ ጂ ኤም) የሴቶች ሀፍረተ ስጋ አካል ጉዳት የሚደርስበት ወይም የአካል መልክ የሚቀይር ተግባር ነው፣ ነገር`ግን ይህ የሚደረግበት የሕክምና ምክንያት የለም። የሴቶችና ልጃገረዶች የረጅም ጊዜ ጤና በከፍተኛ ደረጃ ሊጎዳ ይችላል። በዚህ ተግባር ቀጥተኛ ውጤት ምክንያት በሚፈስ ደም ወይም በሚደርስ ልክፍት የሚሞቱ ሴቶች ይገኛሉ። እንደዚሁም ኤፍ ጂ ኤም ያጋጠማቸው ሴቶች የወሊድ ችግር ሊያጋጥማቸው የሚችልበት ዕድል የላቀ ነው።

ኤፍ ጂ ኤም አብዛኛው ጊዜ የሚፈጸመው በ 5 እና 10 ዕድሜ መካከል በሚገኙ ልጃገረዶች ላይ ነው። ይህ የሴቶች መገረዝ፣ መቁረጥ ወይም ሌሎች ለምሳሌ ሱና፣ ጉድኒን፣ ሃላላይስ፣ ታሁር፣ መግረዝ እንደዚሁም ኪታን የመሰሉትና በሌሎች ስሞችም ይጠራል።

## የኤፍ ጂ ኤም ዓይነቶች፡

ዓይነት 1 – ክሊቶሪስ በከፊል ወይም በመላ ማንሳት።

ዓይነት 2 – ክሊቶሪስና አነስተኛ ላቢያን (ሀፍረተ ስጋን ከበው የሚገኙ "ከንፈሮች") በከፊል ወይም በመላ ማንሳት።

ዓይነት 3 – ክሊቶሪስ የሚያካትት የሴት ሀፍረተ ስጋን በከፊል ወይም በመላ ማንሳት። ጫፍ ጫፉን አያይዞ በመስፋት ትንሽ ቀዳዳ መተው።

ዓይነት 4 – የሴት ሀፍረተ ስጋ መቁረጥ፣ ማቃጠል፣ ፍቆ ማንሳት፣ በሹል ነገር መብሳት፣ መምጠጥ የሚካትቱ ሁሉም ሌሎች የጉዳት ዓይነቶች።

## ኤፍ ጂ ኤም የሚደረግበት ምክንያት ምንድነው?

አብዛኛው ጊዜ የሴት ወላጆች ወይም ዘመዶች ናቸው ኤፍ ጂ ኤም እንዲፈጽምባት የሚያዘጋጁት። የሚፈጸምበት ምክንያቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

- ልማድ
- ሃይማኖት
- ባህል ማስጠበቅ
- ድንግልና ማስጠበቅ
- ንጽህና
- የቤተሰብ ክብር ለመጠበቅ
- ማሕበረሰባዊ ተቀባይነት፣ በተለይ ጋብቻ በሚመለከት

እነዚህ ኤፍ ጂ ኤም የሚፈጸምባቸው ምክንያቶች ካለመረዳት ወይም እውቀት ከማጣት የተነሱ ናቸው።

አንዳንድ ሰዎች፣ ኤፍ ጂ ኤም ለሃይማኖታችን ያስፈልጋል ብለው ያምናሉ፣ ለምሳሌ ዓይነት 1 ኤፍ ጂ ኤም አንዳንድ ጊዜ በስሕተት ሱና ተብሎ ይጠራል። ነገር ግን ኤፍ ጂ ኤምን የሚደግፉ ወይ መደረግ አለበት የሚሉ ጽሑፎች **የሉም**።

## ኤፍ ጂ ኤም ሕገወጥ ነው

ኤፍ ጂ ኤም ሕገወጥ ነው፣ ስለሆነ እዚ አገርም ይሁን ውጭ አገር **በፍጹም** መደረግ የለበትም። እንደዚሁም አንድ ሰው ኤፍ ጂ ኤም እንዲፈጽም በማንኛውም መንገድ መርዳት ሕገወጥ ነው። ይህን ወንጀል ፈጽሞ የተገኘ ማንኛውም ሰው እስከ የ14 ዓመት እስራት፣ ቅጣት (የገንዘብ ቅጣት) ሊሰጠው ይችላል።

## ኤፍ ጂ ኤም ጤናችሁ ላይ ከባድ ጉዳት ያደርሳል

ኤፍ ጂ ኤም የልጃገረዶችና አዋቂ ሴቶች ጤና ላይ ከባድ ጉዳት የሚያደርስ ሲሆን፣ የሚከተሉትን ያካትታል፡

- የማያቋርጥ የሕመም ስሜት
- መምከን ሊያስከትሉ የሚችሉ ተከታታይ ልክፍቶች
- መድማት፣ እባጭና እብጠቶች
- ፈሳሽ ሽንት የመሽናት ወይም የመቆጣጠር ችግሮች
- ጭንቀት፣ ያሰቃቂ ተሞክሮዎች ምስል ማስታወስ፣ ራስን መጉዳት
- ሞት ሊያስከትሉ የሚችሉ የማማጥ/ወሊድ ችግሮች

## ምን ዓይነት እርዳታ ማግኘት ትችላላችሁ?

ኤፍ ጂ ኤም የደረሰባችሁ ከሆናችሁ፣ ከሐኪማችሁ ወይም ማንኛውም የጤና ክብካቤ ባለሙያ የሕክምና እገዛና ድጋፍ ማግኘት ትችላላችሁ። እርጉዝ ከሆናችሁ ከአዋላጅ እገዛ ማግኘት ትችላላችሁ።

እንደዚሁም የኤፍ ጂ ኤም ልዩ የጤና ማዕከሎችና አገልግሎቶች ዝርዝር መረጃ የሚከተለው ጋር ማግኘት ትችላላችሁ www.nhs.uk/fgm

**ኤፍ ጂ ኤም ሊያጋጥማት የሚችልበት ማንኛውም ስጋት ያላት ልጃገረድ በሚመለከት የሚያሳስባችሁ ነገር ካለ፣ ሕክምና ለሚሰጣችሁ ባለሙያ ያሳውቁ፣ ወይም ወደ የኤን ኤስ ፒ ሲ ሲ (NSPCC) የእገዛ መስመር በቀን ለ24 ሰዓታት ወደ 0800 028 3550 ይደውሉ።**

**ሴት ልጃችሁ ላይ ኤፍ ጂ ኤም ለመፈጸም የቤተሰብ ወይም የማሕበረሰብ ተጽዕኖ በሚመለከት የሚያሳስባችሁ ነገር ካለ፣ ከሐኪማችሁ፣ ከበጤና ምክንያት ሊጠይቃችሁ የሚመጣ ሰራተኛ ወይም ከማንኛውም የጤና ክብካቤ ባለሙያ እገዛ ይጠይቁ።**

## የጤና ፓስፖርት

*የ ‘የሴቶች ህፍረተ ስጋ መገረዝን የሚቃወም የጽሑፍ ቃል’ ቅጂ እንዲሰጣችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ። ይህ ለኪስ የተዘጋጀ የጽሑፍ ቃል ሲሆን፣ ወደ ውጪ አገር ስትሄዱ ይዛችሁት ልትሄዱ የምትችሉ በ11 ቋንቋዎች ተጽፎ የሚገኝ ነው። ለቤተሰቦቻችሁ ማሳየት ትችላላችሁ። የኤፍ ጂ ኤም ተግባር፣ ዩከይ ውስጥ፣ ከባድ ወንጀል መፈጸም ማለት መሆኑን ግልጽ የሚያደርግ ነው።*

## ኤፍ ጂ ኤም ካጋጠማቸው ታካሚዎች መረጃ መሰብሰብና ጥቅም ላይ ማዋል

ኤፍ ጂ ኤም የሚመለከት መረጃ፣ በጤናና ማሕበራዊ ክብካቤ መረጃ ማዕከል ኤች ኤስ ሲ ኣይ ሲ (HSCIC) ይሰበሰባል። ምን ዓይነት መረጃ እንደምንሰበስብ፣ ለምን ምክንያት እንደሆነ፣ በምን ዓይነት መንገድ ጥቅም ላይ እንደምናውለው ወይም መረጃችሁ በዚህ ዓይነት መንገድ ጥቅም ላይ እንዳይውል ለመቃወም በሚመለከት በተጨማሪ ለማወቅ፣ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት እባክዎን የሚከተለውን ይጎብኙ
www.hscic.gov.uk/patientconf

**ስለ ኤፍ ጂ ኤም ተጨማሪ መረጃ ከፈለጋችሁ፣ እባክዎን የሚከተለውን ይጎብኙ**
**www.nhs.uk/fgm**

© Crown copyright 2015
2903740 04/2015
በውልያምስ ሊ ለጤና ክፍል የተዘጋጀ
www.dh.gov.uk/publications